በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቅርስ ጥበቃናእንክብካቤ

# የሙያ ዘርፎች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 484/2013

# የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ

## የሙያ ዘርፎች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 484/2013

ቅርስ ጥበቃ እንክብካቤ-ጥገና ተግባር ልዩ የሆነ ዕውቀትና ክህሎት፣ እንዲሁም ብዝሃ የሙያ ሥብጥር ያላቸውን ባለሙያዎች የቡድን ሥራ የሚጠይቅ በመሆኑ፤

በሀገራችን በዓይነትና በብዛት ተሰራጭተው የሚገኙ ቅርሶችን የሚንከባከቡና እና የሚጠግኑ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ባለሙያዎች ቁጥር ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ያንዣበቡባቸውን ቅርሶች ጠብቆ፣ ተንከባክቦ፣ ጠግኖና አልምቶ ለአሁኑ ትውልድ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታን እየሰጡ ወደ መጪው ትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ብቃታቸው የተረጋገጠ ባለሙያዎች ማፍራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሀገሪቱ የሚገኙትን ቅርሶችን መጠበቅ፣ መንከባከብና መጠገን በመንግሥት አቅም ብቻ የማይከናወን በመሆኑ፣ በግሉ ዘርፍ በሙያው ለተሰማሩ ባለሙያዎች ተገቢውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ለዘርፉ አጋር ኃይል እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በዓለም አቀፍ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ስምምነቶችና ቻርተሮች መሰረት የሚከናወኑ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ተግባራት የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ መርሆዎችን የተከተለ መሆን ስላለበት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ከሥራ ጥራት እና ብቃት አንፃር ለመቆጣጠር የሚያስችል መመዘኛ መስፈርት ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ የሙያ ዘርፎች የብቃት ማረጋገጥ ተግባር ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ ወጥነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 19 እና 46(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## <u>ጠቅላላ</u>

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ መመሪያ "የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ የሙያ ዘርፎች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 484/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

   1) "አዋጅ" ማለት የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 ነው፡፡
   2) በአዋጁ አንቀፅ 3 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
   3) "ዋና ዳይሬክተር" ማለት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡
   4) "አመልካች" ማለት የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ - ጥገና ዘርፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት፣ ለማሳደስ ወይም ደረጃ ለማሳደግ የሚያመለክት ባለሙያ ነው፡፡
   5) "የምስክር ወረቀት" ማለት በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ - ጥገና የሙያ ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሙያዎች የሚሰጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ነው፡፡
   6) "የመረጃ ቋት" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ - ጥገና የማማከር አገልግሎት ለመስጠት እና በቅርስ ጥገና የሥራ ዘርፍ ለመሰማራት የተመዘገቡና ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ ባለሙያዎች ወይም ሙያተኞች ወይም ጠጋኞች ዝርዝር የያዘ ቋት ነው፡፡
   7) "የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ - ጥገና" ማለት ተፈጥሮአዊ በሆነ ሂደትና ለውጥ ወይም በሰው ሰራሽ መንስኤዎች አማካኝነት በቅርሶች ላይ የደረሰውን፣ እየደረሰ ያለውን ወይም ሊደርስ የሚችለውን የጉዳት ሁኔታ በጥልቀት በመፈተሽ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለማስወገድ፣ ለመቀነስ ወይም ለማቃለል ጥንታዊ ይዘትና ሁኔታቸው ሳይቀየር ለቅርሶች የሚደረግ አጠቃላይ የጥበቃና እንክብካቤ - ጥገና ተግባር ነው፡፡
   8) "ባለሥልጣን" ማለት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡
   9) "ዳይሬክቶሬት" ማለት የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡
   10) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
   11) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ - ጥገና ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ አግኝተው በማማከርና በጥገና ሥራ እንዲሰማሩ በማድረግ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ሽፋንን ማሳደግ ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙና በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ - ጥገና የሙያ ዘርፍ በተሰማሩ ባለሙያዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# ስለብቃት ማረጋገጫ ደረጃ፣ መስፈርትና ማመልከቻ

## 5. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1) ማንኛውም ባለሙያ ከባለሥልጣኑ የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲኖረው ብቻ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና የሙያ ዘርፎች መሰማራት ይችላል፡፡
2) ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ ለሚቀርብ አመልካች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 6. የብቃት ማረጋገጫ ደረጃዎችና መስፈርቶች

1) በባለሥልጣኑ የሚሰጡ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች የሚከተሉት ደረጃዎችና መስፈርቶች ይኖሯቸዋል፡-

**ሀ. ደረጃ 1**፡-የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ባለሙያ

1. በመመሪያው አባሪ 1 /አንድ/ ለደረጃው በተዘረዘሩት የትምህርት መስኮች ዲግሪና የሥራ ልምድ ያለው፣
2. በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና መርህ የተግባር ሥራ ላይ የጠለቀ ዕውቀት ያለውና ለዚህም ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣

3. ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ስታንዳርዶችን ጠንቅቆ የሚያውቅና የማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፣

ለ. **ደረጃ** 2፡- የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ባለሙያ

1. በመመሪያው በአባሪ 1 /አንድ/ ለደረጃው በተዘረዘሩት የትምህርት መስኮች ዲፕሎምና የሥራ ልምድ ያለው፣
2. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና መርህዎችና ስታንዳርዶችን ጠንቅቆ የሚያውቅና እነዚህን መሰረት በማድረግ ስላከናወናቸው የቅርስ እንክብካቤና ጥገና ተግባራት ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

ሐ. **ደረጃ** 3፡-የቅርስ ጠጋኝ ባለሙያ

1. በመመሪያው በአባሪ 1 /አንድ/ ለደረጃው በተዘረዘረው የትምህርት መስክ ዲፕሎምና የሥራ ልምድ ያለው፣
2. መሰረታዊ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና መርህዎችን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሆኖ በቅርስ ጥበቃና እንክበካቤ-ጥገና ሙያ ልምድ ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ማንኛውም አመልካች ለሚያመለክትበት የተለየ የሙያ ዘርፍ በአባሪ ሁለት (2) የተዘረዘሩትን ተጨማሪ መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል፣

7. <u>**ደረጃ ስለተሰጣቸው ባለሙያዎች**</u>

1) የደረጃ 1 ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ባለሙያ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና የማማከር አገልግሎትና የቅርስ ጥገና ስራ ላይ መሰማራት ይችላል፡፡
2) ደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ሙያተኛ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ጥናት መሰረት የደረጃ አንድ የብቃት ማረጋገጫ በተሰጠው ባለሙያ ምክር፣ ድጋፍና ክትትል እየተደረገበት በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ስራ ላይ መሰማራት ይችላል፡፡
3) የደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ባለሙያ በቅርስ ባለሙያ የጥገና ጥናት መሰረት የደረጃ 1 ወይም የደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠውን ባለሙያ በማገዝ የቅርስ ጥገና ተግባር ላይ መሰማራት ይችላል፡፡

## 8. <u>የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1) የብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት የሚፈልግ ማንኛውም አመልካች ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገውን የማመልከቻ ፎርም በመሙላት የሚከተሉትን ማስረጃዎች ከፎቶ ኮፒ ጋር አሟልቶ በግንባር ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

   ሀ. የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት፣

   ለ. እንደሚያመለክትበት የብቃት ማረጋገጫ ደረጃ በአባሪ አንድ (1) በተዘረዘሩት የትምህርት መስኮች ያገኛቸውን የዲግሪ፣ ዲፕሎማ ወይም ሰርተፍኬት የትምህርት ማስረጃ፣

   ሐ. የቅርስ ጥገና ጥናት ወይም የቅርስ ጥገና ወይም ጥበቃና እንክብካቤ የሥልጠና ሰርፊኬት ወይም ዓለም አፍም ስታንዳርድ የጠበቀ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ሰርተፍኬት ወይም በመደበኛ የትምህርት ዝግጅቱ እነዚህን የትምህርት አይነቶች ስለመውሰዱ የሚገልፅ ማስረጃ፣

   ሠ. እንደሚያመለክትበት ደረጃ በአባሪ 1 /አንድ/ የተገለፁት ተፈላጊው የሥራ ልምድ እንዳለው የሚገልፅ ማስረጃ፣

   ረ. 3 × 4 የሆነ ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ

2) የቀረበው የትምህርት ማስረጃ ከውጭ ሀገር የተገኘ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የአቻ ግምት ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡

3) በትምህርት ማስረጃነት የቀረበው ዲግሪ ጊዜያዊ ከሆነ ከተሰጠ አምስት ዓመት ያላለፈው መሆን አለበት፡፡ አምስት ዓመት ያለፈው ከሆነ ከተሰጠበት ተቋም ዋናውን የትምህርት ማስረጃ አለመሰጠቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 9. <u>የብቃት ማረጋገጫ ለማሳደስ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ የፈለገ ማንኛውም አመልካች ለዚሁ ተግባር ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገውን ፎርም በመሙላት፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት፣ 3 × 4 የሆነ ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የቀድሞውን የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በመያዝ በግንባር ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት መቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(3) መሰረት ጊዜያዊ የትምህርት ማስረጃ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የወሰደ ባለሙያ የብቃት ማረጋገጫው ካገኘ አምስት ዓመት ካለፈው ለእድሳት ሲመጣ ዋናውን ማቅረብ አለበት፡፡ ዋናውን የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ የማይችል ከሆነ ባለፉት አምስት ዓመታት ማስረጃው በተቋሙ አለመሰጠቱን የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

3) አመልካቹ ቀደም ሲል ስላከናወናቸው ሥራዎች ሪፖርት ወይም ካሰራው አካል የተሰጡ የመልካም አፈፃፀም ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፤

## 10. የብቃት ማረጋገጫ ደረጃን ለማሳደግ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1) ማንኛውም የብቃት ደረጃን ለማሳደግ የሚፈልግ አመልካች ለዚሁ ተግባር በመመሪያው አባሪ የተደረገውን ፎርም በመሙላት የሚከተሉት መረጃዎች በማያያዝ በግንባር ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት መቅረብ አለበት፡-

ሀ. በዚህ መመሪያ መሠረት ማደግ ለሚፈልግበት ደረጃ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላቱን የሚገልጽ ማስረጃ፤

ለ. የቀድሞውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

ሐ. ቀድም ሲል ስላከናወናቸው ሥራዎች ሪፖርት ወይም ካሰራው አካል የተሰጡ የመልካም አፈፃፀም ማስረጃ፤

መ. 3×4 የሆነ ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፤

2) በመጀመሪያ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ /አንድ/ አመት ወይም ከዛ በላይ የሆነ ጊዜ ሳይሞላው የሚቀርብ ደረጃን የማሳደግ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## 11. ስለምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1) ባለሥልጣኑ አስፈላጊውን መመዘኛዎች አሟልቶ ለሚቀርብ አመልካች ከአምስት የሥራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

2) ማመልከቻው በአግባቡ ያልቀረበ ከሆነ ወይም አስፈላጊ መመዘኛዎችን ያላሟላ ሆኖ ከተገኘ የተጓደለውን ማስረጃ አሟልቶ እንዲያቀርብ ለአመልካቹ በፅሁፍ ይገለፅለታል፡፡

12. <u>ስለምስክር ወረቀቱ ይዘት</u>

በባለስልጣኑ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንደ አግባቡ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

1) የባለሙያውን ሙሉ ስም፣
2) የሥራ አድራሻ፣
3) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠበት የማማከርና የመተግበር አገልግሎት ዘርፍ፣
4) የምስክር ወረቀቱ ደረጃ፣
5) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፣
6) የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ፣
7) የባለሙያውን ፎቶ ግራፍ፣
8) መለያ ቁጥር
9) የፈቃድ ሰጪው ኃላፊ ሥም፣ ፊርማና የባለስልጣን መ/ቤቱ ማህተም፣

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የብቃት ማረጋገጫ አፈፃፀምና መብትና ግዴታዎች</u>

13. <u>ዳይሬክቶሬቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት፣ ለማደስ ወይም ለማሳደግ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይቀበላል፡፡
2) የቀረቡ ማመልከቻዎችን በመመሪያው በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት መቅረባቸውንና ትክክለኛ መሆናቸውን በመገምገም ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
3) የቀረቡ ማመልከቻዎች ያልተሟሉ ሆነው ከተገኙ ተሟልተው እንዲቀርቡ ለአመልካቹ ያሳውቃል፤
4) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ በሥራ አፈፃፀሙ ሙያው የሚጠይቀው ብቃት የሌለው ወይም ተግባሩን በአግባቡ የማይወጣ ስለመሆኑ በማስረጃ ሲያረጋግጥ የምስክር ወረቀቱ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

5) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በመጥፋቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት እንደገና እንዲተካ የቀረበ ማመልከቻን በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፣
6) የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸውን፣ የታደሰላቸውን እንዲሁም ደረጃቸውን ያሳደጉ ባለሙያዎችን ዝርዝር መረጃ የሚገልጽ የመረጃ ቋት ያዘጋጃል፤ ቋቱንም በየጊዜው ወቅታዊ ያደርጋል፤

## 14. <u>የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ባለሙያ መብቶች</u>

የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ባለሙያ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1) ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችና ቀደም ሲል የተከናወኑ ጥናቶችና ሪፖርቶችን ከባለሥልጣኑ የማግኘት፣
2) ደረጃውን የጠበቀ የጥበቃና እንክብካቤ ጥናትና ሥራ ሲያከናውን ውጤቱን የማሳተም፣
3) ለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥናትና የጥገና ሥራ አጋዥ የሆኑ ቁሳቁሶችና ኬሚካሎች ከውጭ ሀገር ሲያስገባ ከባለስልጣኑ የድጋፍ ደብዳቤ የማግኘት፣

## 15. <u>የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ባለሙያ ግዴታዎች</u>

1) በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥናት እና የጥገና ሥራ ወቅት ለቅርሱና ቅርሱ ለሚገኝበት አካባቢ ማህበረሰብ የሚገባውን ክብር የመስጠት፣
2) በጥበቃና እንክብካቤ ጥናትና የጥገና ሥራ ወቅት ዓለም አቀፍ የሆኑ የጥገና መርህዎችና ፍልስፍናዎችን የመተግበር፣
3) ከባለስልጣኑ ወይም ከሚመለከተው ክልል ተወክሎ ለክትትልና ቁጥጥር ሥራ ለሚሠማራ ባለሙያ አስፈላጊውን መረጃ የመስጠትና የመተባበር፣
4) በተሰጠው የብቃት ማጋገጫ ደረጃ ብቻ ተግባሩን የማከናወን፣
5) ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ሙሉ መረጃ የያዘ ሰነድ የማዘጋጀት፣
6) ስለሚከናውናቸው ተግባራት ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፣
7) የተሰጠውን ፈቃድ ከባለስልጣኑ እውቅና ውጪ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት፣
8) በመመሪያው በተገለፀው የጊዜ ገደብ መሰረት ያገኘውን ፈቃድ የማደስ፡፡
9) ብቃት ማረጋገጫ ሲሰጠው የተመዘገቡ የአድራሻና ሌሎች መረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች ሲኖሩ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ፡፡

16. <u>ክትትልና ቁጥጥር ስለማድረግ</u>

1) ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው ክልል የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ባለሙያ በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ መሠረት ተግባሩን እያከናወነ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
2) ባለሙያው ከተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ውጪ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ከተገኘ በዚህ መመሪያ መሠረት ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

17. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

18. <u>ስለብቃት ማረጋገጫ እድሳት</u>

1) ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡
2) ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በባለሥልጣኑ ተመዝግበው በቅርስ ጥበቃ እንክብካቤ-ጥገና የተሰማሩ ባለሙያዎች በዚህ መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማውጣት ይኖርባቸዋል፡፡

19. <u>የጠፋ ወይም የተበላሸ የምስክር ወረቀትን ስለመተካት</u>

1) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ዋና ቅጂ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ባለሙያ ለዚሁ ተግባር በባለስልጣኑ ያዘጋጀውን ፎርም ሞልቶ በምትኩ ሌላ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡
2) የጠፋ የምስክር ወረቀትን ለመተካት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር አግባብ ካለው የሕግ አስፈፃሚ አካል ምስክር ወረቀቱ መጥፋቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡

## 20. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ</u>

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊታገድ ይችላል፡-
   ሀ. ባለሙያው ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር በመጣስ ስራውን ተገቢ ባልሆነ አሰራር ያከናወነ ስለመሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣
   ለ. ባለሙያው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 18 መሠረት የተጣሉ ግዴታዎች ተላልፎ ከተገኘ
2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ባለሙያ ላይ የሚጣለው የእገዳ እርምጃ የሚቆየው እንደጥፋቱ ክብደት እስከ 6 ወራት ሊቆይ ይችላል፣
3) እገዳው ሊነሳ የሚችለው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 በ "ሀ" እና "ለ" የተጠቀሱ ጉድለቶች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መስተካከላቸው ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

## 21. <u>የምስክር ወረቀት ስለመሠረዝ</u>

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሰረዝ ይችላል

1) የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፣
2) የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ በራሱ ፈቃድ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስ፣
3) ባለሙያው የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማጭበርበር መሆኑ ከተረጋገጠ፣
4) የምስክር ወረቀቱ ለሶስተኛ ወገን ሰው ተላልፎ ከተገኘ፣
5) ባለሙያው በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከተሰጠው ደረጃና ፈቃድ ውጪ ሎሎች ተግባራት ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፤
6) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 መሠረት የምስክር ወረቀቱን ያሳገዱ ምክንያቶች እገዳው በተጣለ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ካልተስተካከሉ ከሆነ፤

22. <u>ስለቅሬታ አቀራረብ</u>

1) በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ለቅሬታው መነሻ የሆነው ውሳኔ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 /አምስት/ የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ የተገልጋዮች ቅሬታ ማስተናገጃ ክፍል በፅሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2) የተገልጋዮች ቅሬታ ማስተናገጃ ክፍሉ ጥያቄው በቀረበ በ5 /አምስት/ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ምላሽ መስጠት አለበት፡፡
3) በቅሬታ ማስተናገጃ ክፍሉ ምላሽ ያልረካ ተገልጋይ አቤቱታውን በ10 /አሥር/ የሥራ ቀናት ውስጥ ለዋና ዳይሬክተሩ በፅሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
4) ዋና ዳይሬክተሩ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔውን በ10 /አስር/ የሥራ ቀናት ያሳውቃል፤

23. <u>የሥራ ማንዋል ስለማውጣት</u>

ባለሥልጣኑ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም ዝርዝር የሥራ ማንዋል ሊያወጣ ይችላል፡፡

24. <u>ቅጣት</u>

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

25. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎችና ልማዳዊ አሠራሮች</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

26. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

27. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከመስከረም 04 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

# አባሪ 1. መስፈርቶች

## <u>ደረጃ አንድ፡-የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ባለሙያ</u>

## 1. 1. ዝቅተኛመስፈርት

*ሀ. የመጀመሪያ ዲግሪ*

*ለ. ከመጀመሪያ ዲግሪ በኋላ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና 10 ዓመት የሥራ ልምድ*

*ሐ. ከሁለተኛዲግሪበኋላ 8 ዓመትየሥራልምድ*

*መ. ከ3ኛ ዲግሪ በኋላ 6 ዓመት የሥራ ልምድ*

*ሠ. የስራ ልምዱ የሰራቸውን ስራዎች የሚያሳይ 4 ሰነድ/ ሪፖርት ማቅረብ የሚችልና፣ በአንዱፕሮጀክት ላለፉት አምስት ዓመታት የተከናወነ መሆን ይኖርበታል*
*ረ. በዓለም አቀፍ ስታንዳርድ (ኢክሮም) መሰረት በተለያዩ የቅርስጥበቃና እንክብካቤ- ጥገና ዘርፎች የሚሰጠውን ሥልጠና ያጠናቀቀ ሆኖ፣ ስምንት(8) አመት የተግባር ሥራ ልምድ ያለው፤ ይህንንም አራት ያከናወናቸውን የጥበቃናእንክብካቤ -ጥገና ስራዎችን የሚያረጋግጥ ሰነድ /ሪፖርት) ማቅረብ የሚችል፡፡*

**የታሪካዊ ግብረ ህንጻዎች ኮንሰርቫተር /historic building conservator)**

**የመነሻ የትምህርት መስኮች**

- ስትራክቸራል ኢንጂነር/structural engineer
- ሲቪል ኢንጂነር/civil engineer
- አርክቴክት/architect
- አርኪዮሎጂስት/archaeologist
- የታሪክ ባለሙያ/historian
- አርክቴክት ኮንሰርቫተር/ architect conserevator
- ኢንቫይሮመንታል መሃንዲስ/environmental engineer
- ጂኦሎጂስት/geologist

1.2አርቲፋክት ኮንሰርቫተር/ ኦብጀክት ኮንሰርቫተር /artifact or object conservator

**የመነሻ የትምህርት መስኮች**

- አርኪዎሎጂስት/archaeologist
- የእንጨት ኮንሰርቫተር/wood conservator
- የድንጋይ ኮንሰርቫተር/stone conservator
- የጨርቃ ጨርቅ ኮንሰርቫተር/textile conservator
- ኬሚካል ኢንጂነር/ ኬሚስት/ chemical engineer
- ፊዚስት/ physicist
- ፍሬም ኮንሰርቫተር/frame conservator
- ሴራሚክ ኮንሰርቫትር/ ceramic conservator
- ኪዩሬተር/ curator
- Entomologist/museum integrated pest management
- ግላስ ኮንሰርቫተር/ glass consrvator

**1.3 አርትኮንሰርቫተር፣/ art conservator/ wall painting conservator**

**የመነሻ የትምህርት መስኮች**

- የስዕል ኮንሰርቫተር/ painting conservator
- አርትሂስቶሪያን/ art historian
- ሰዓሊ አርቲስት/ painter
- ሪስቶረር/ restorer
- የዋሻ ላይ ስዕሎ ችኮንሰርቫተር
- አርኪዮሎጂስት/ archaeologist
- የቅድመ ታሪክ ባለሙያ/ prehistorian

## 1.4 የቅርስ ኮንሰርቫተር /የቅርስ አስተዳደር/ heritage conservator/ heritage management

**የመነሻ የትምህርት መስኮች**

- ሙዚየም ኪዩሬተር/ museum curator
- የስብስብ ኪዩሬተር/ collection curator
- አርኪዎሎጂስት/ archaeologist
- ዶክመንታሪ ሊንጉስቲክ እና ባህል\ documentary linguistic and culture
- ሙዚዮሎጂስት/ museologist
- የታሪክባለሙያ/ historian
- አንትሮፖሎጂስት/ anthropologist

## 1.5. የመካነ ቅርስ ቦታዎች ኮንሰርቫተር/ site conservator

**የመነሻ የትምህርት መስኮች**

- አርኪዎሎጂስት/ archaeologist
- የታሪካዊ ቦታዎች ኮንሰርቫተር/ historic garden conservator
- የተፈጥሮ አካባቢ መሃንዲስ/ environmental engineer
- የቅርስ ኮንሰርቫተር/ heritage conservator/ heritage science
- የታሪክ ባለሙያ/ historian
- አንትሮፖሎጂስት/ anthropologist
- የዋሻ ውስጥ ስዕሎች ጠጋኝ/ cave art restorer

# ደረጃ-ሁለት፡-የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና ሙያተኛ

**ዝቅተኛ መስፈርት**

ሀ. ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ትምህርት መስኮች ዲፕሎማ ያለው ሆኖ በቅርስ ጥበቃናእንክብካቤ-ጥገና 10 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ሆኖ፣ ይህን የሚያረጋግጥ 3 የሰነድ / ሪፖርት/ ማቅረብ የሚችል፣

ለ. ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ትምህርት መስኮች የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሆኖ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ- ጥገና ስራ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ- ጥገና 8 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ሆኖ፣ ይህን የሚያረጋግጥ 3 የሰነድ / ሪፖርት/ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

ሐ. ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ትምህርት መስኮች ሁለተኛ ዲግሪ ያለው ሆኖ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ- ጥገና ስራ በቅርስ ጥበቃናእንክብካቤ- ጥገና 6 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ሆኖ፣ ይህን የሚያረጋግጥ 3 የሰነድ / ሪፖርት/ ማቅረብ የሚችል፣

**የታሪካዊግብረህንጻዎችኮንሰርቫተር/ አርክቴክትኮንሰርቫተር/historic building conservator**

**የትምህርት መስኮች**

- ስትራክቸራልኢንጂነር/structural engineer
- ሲቪልኢንጂነር/civil engineer
- አርክቴክት/architect
- አርኪዮሎጂስት/archaeologist
- የታሪክባለሙያ/historian
- አርክቴክትኮንሰርቫተር/ architect conserevator
- ኢንቫይሮመንታልመሃንዲስ/environmental engineer
- ጂኦሎጂስት/geologist
- የህንጻግንባታባለሙያ

**አርቲፋክትኮንሰርቫተር/ ኦብጀክትኮንሰርቫተር/artifact or object conservator**

በስሩመያዝየሚገባቸውሙያተኞች

- የእንጨትኮንሰርቫተር/wood conservator
- አርኪዖሎጂስት/archaeologist
- የድንጋይኮንሰርቫተር/stone conservator
- የጨርቃጨርቅኮንሰርቫተር/textile conservator
- ኬሚካልኢንጂነር/ ኬሚስት/ chemical engineer
- ፊዚስት/ who specialize in physics
- ፍሬምኮንሰርቫተር/frame conservator

- ሴራሚክኮንሰርቫተር/ ceramic conservator
- ኪዩሬተር/ curator
- Entomologist/museum integrated pest management
- ግላስኮንሰርቫተር/ glass consrvator

**አርትኮንሰርቫተር፣/ art conservator/ wall painting conservator**

**የትምህርት መስኮች**

- የስዕልኮንሰርቫተር/ painting conservator
- አርትሂስቶሪያን/ art historian
- ሰዓሊአርቲስት/ painter
- ሪስቶረር/ restorer
- የዋሻላይስዕሎችኮንሰርቫተር
- አርኪዮሎጂስት/ archaeologist
- የቅድመታሪክባለሙያ/ prehistorian

**የቅርስኮንሰርቫተር/ የቅርስአስተዳደር/ heritage conservator/heritage management**

**የትምህርት መስኮች**

- ሙዚየምኪዩሬተር/ museum curator
- የስብስብኪዩሬተር/ collection curator
- አርኪዖሎጂስት/ archaeologist
- ዶክመንታሪሊንጉስቲክእናባህል\ documentary linguistic and culture
- ሙዚዮሎጂስት/ museologist
- የታሪክባለሙያ/ historian
- አንትሮፖሎጂስት/ anthropologist

**የመካነ ቅርስ ቦታዎች ኮንሰርቫተር/ site conservator**

የትምህርት መስኮች

- አርኪዎሎጂስት/ archaeologist
- የታሪካዊቦታዎችኮንሰርቫተር/ historic garden conservator
- የተፈጥሮአካባቢመሃንዲስ/ environmental engineer
- የቅርስኮንሰርቫተር/ heritage conservator/ heritage science
- የታሪክባለሙያ/ historian
- አንትሮፖሎጂስት/ anthropologist
- የዋሻ ውስጥ ስዕሎችጠጋኝ/ cave art restorer

# ደረጃ-ሶስት፡-የቅርስ ጠጋኝ

ዝቅተኛመስፈርት

ሀ. ሌቭል 2

ለ. ከ ሌቭል 2 በኋላበቅርስጥበቃናእንክብካቤ-ጥገና 8 ዓመትየሥራልምድ

ሐ. ከ ሌቭል 3 በኋላበቅርስጥበቃናእንክብካቤ-ጥገና 6ዓመትየሥራልምድ

መ. ከ ሌቭል4በኋላበቅርስጥበቃናእንክብካቤ-ጥገና 4ዓመትየሥራልምድ

**መስኮች**

- ግንበኛ/construction technology/ building/

- የእንጨትሰራተኛ/ wood worker

- የቆዳሰራተኛ/ tanner

- ብረታብረትሰራተኛ/ general metal

- ቀያሽ/ surveyer

-የሽመና ሰራተኛ/ weaver

- የእደ ጥበብ ሰራተኛ/ handcraft

- አናጺ/ carpenter

አባሪ 2

፡ በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ-ጥገና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጣቸው የትምህርት መስኮች እና ተፈላጊ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ዘርፎች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | ተያያዥነት ያለው የሥራ ልምድ (በዓመት) | ያዘጋጃቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ ዘገባዎች | የአጭር ጊዜ ስልጠና | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የስዕላዊ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ጥናት አጥኚ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ 1 | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ | - | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገና ጥናት ዘርፍ የተወሰደ ስልጠና | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |
| | | ጀማሪ አማካሪ 2 | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለዲፕሎማ 8 - 10<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 6 -8<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 1 | ቢ.ያንስ አንድ | | |
| | | አማካሪ | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢ.ያንስ ሁለት | | |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | ቢ.ያንስ አራት | | |
| 2 | የስዕላዊ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ተግባር ከዋኝ ባለሙያ | ጀማሪ ከዋኝ (ጠጋኝ) 1 | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገናናእንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 5 - 7<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 - 5<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | - | | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |
| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ዘርፎች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | ተያያዥነት ያለው የሥራ ልምድ (በዓመት) | ያዘጋጃቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ ዘገባዎች | የአጭር ጊዜ ስልጠና | ሌሎች |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጀማሪ ከዋኝ (ጠጋኝ) 2 | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገናናእንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 4 - 6<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 2- 4<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 5<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 1 | ቢያንስ አንድ | በአርት ጥገናና እንክብካቤ ዘርፍ የተወሰደ ስልጠና | |
| | | ከዋኝ (ጠጋኝ) | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢያንስ ሁለት | | |
| | | ከፍተኛ ከዋኝ(ጠጋኝ) | በስዕላዊ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | ቢያንስ አራት | | |
| 3 | የቅርፃቅርስ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ጥናት አጥኚ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ 1 | በቅርፃቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 5 - 8<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -5<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | - | በቅርፃ ቅርፅ ጥገናና እንክብካቤ ጥናት(sculpture) ዘርፍ የተወሰደ ስልጠና | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |
| | | ጀማሪ አማካሪ 2 | በቅርፃቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 5-8<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -5<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 1 | ቢያንስ አንድ | | |
| | | አማካሪ | በቅርፃቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢያንስ ሁለት | | |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በቅርፃቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | ቢያንስ አራት | | |

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ዘርፎች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | ተያያዥነት ያለው የሥራ ልምድ (በዓመት) | ያዘጋጃቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ ዘገባዎች | የአጭር ጊዜ ስልጠና | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የቅርፃቅርስ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ተግባር ከዋኝ(ጠ.ጋኝ) ባለሙያ | ጀማሪ ከዋኝ (ጠ.ጋኝ) 1 | በቅርፃቅርስ ጥገናናእንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 5 - 8<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -5<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | - | በቅርጻቅርፅ ጥገናና እንክብካቤ ዘርፍ (sculpture)የተወሰደ ስልጠና | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |
| | | ጀማሪ ከዋኝ (ጠ.ጋኝ) 2 | በቅርፃቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 6 -8<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 1 | ቢ.ያንስ አንድ | | |
| | | ከዋኝ (ጠ.ጋኝ) | በቅርፃቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢ.ያንስ ሁለት | | |
| | | ከፍተኛ ከዋኝ (ጠ.ጋኝ) | በቅርፃቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | ቢ.ያንስ አራት | | |
| 5 | የእንጨት ውጤት የሆኑ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ጥናት አጥኚ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ 1 | በእንጨት ኮንሰርቬሽን ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 5 - 8<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -5<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | - | በእንጨት ጥገና(wood conservation) ዘርፍ የተወሰደ ስልጠና | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |
| | | ጀማሪ አማካሪ 2 | በእንጨት ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 6 -8<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 1 | ቢ.ያንስ አንድ | | |
| | | አማካሪ | በእንጨት ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢ.ያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢ.ያንስ ሁለት | | |

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ዘርፎች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | ተያያዥነት ያለው የሥራ ልምድ (በዓመት) | ያዘጋጃቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ ዘገባዎች | የአጭር ጊዜ ስልጠና | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በእንጨት ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | ቢያንስ አራት | | |
| 6 | የእንጨት ውጤት የሆኑ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ተግባር ከዋኝ ባለሙያ | ጀማሪ ከዋኝ (ጠጋኝ) 1 | በእንጨት ውጤቶች ጥገናናእንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 8-10<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 5 -8<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | - | የእንጨት ውጤት በሆኑ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ጥናት ዘርፍ የተወሰደ ስልጠና | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |
| | | ጀማሪ ከዋኝ (ጠጋኝ) 2 | በእንጨት ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 8-10<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 5 -8<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 1 | ቢያንስ አንድ | | |
| | | ከዋኝ (ጠጋኝ) | በእንጨት ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢያንስ ሁለት | | |
| | | ከፍተኛ ከዋኝ (ጠጋኝ) | በእንጨት ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | ቢያንስ አራት | | |
| 7 | የጨርቃጨርቅ ውጤት የሆኑ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ጥናት አጥኚ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ 1 | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናናእንክብካቤጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 2 - 4<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -4<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | - | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ(textile conservation)ጥናት ዘርፍ የተወሰደ ስልጠና | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |
| | | ጀማሪ አማካሪ 2 | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 2 - 4<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -4<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 1 | ቢያንስ አንድ | | |

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ዘርፎች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | ተያያዥነት ያለው የሥራ ልምድ (በዓመት) | ያዘጋጃቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ ዘገባዎች | የአጭር ጊዜ ስልጠና | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካሪ | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 6 -8<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢያንስ ሁለት | | |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 7<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 5 | ቢያንስ አራት | | |
| 8 | የጨርቃጨርቅ ውጤት የሆኑ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ተግባር ከዋኝ ባለሙያ | ጀማሪ ከዋኝ (ጠጋኝ) 1 | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናናእንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 5 - 8<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -5<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | - | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ(textile conservation) ዘርፍ የተወሰደ ስልጠና | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |
| | | ጀማሪ ከዋኝ (ጠጋኝ) 2 | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 6 -8<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 1 | ቢያንስ አንድ | | |
| | | ከዋኝ (ጠጋኝ) | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢያንስ ሁለት | | |
| | | ከፍተኛ ከዋኝ (ጠጋኝ) | በጨርቃጨርቅ ውጤቶች ጥገናና እንክብካቤ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | ቢያንስ አራት | | |
| 9 | የታሪካዊ ህንፃዎች ጥገናና እንክብካቤ ጥናት ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ 1 | በቅርስ ጥበቃና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 5 - 8<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -5<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | | በቅርስ ጥገናና እንክብበቤ (Heritage Conservation)ዘርፍ የተወሰደ ስልጠና | የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ |

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ዘርፎች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | ተያያዥነት ያለው የሥራ ልምድ (በዓመት) | ያዘጋጃቸው የቅርስ ጥገና ጥናት ወይም ተመሳሳይ ዘገባዎች | የአጭር ጊዜ ስልጠና | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጀማሪ አማካሪ 2 | በቅርስ ጥበቃና<br>በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 9 - 10<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 6<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | ቢያንስ አንድ | | |
| | | አማካሪ | በአርክቴክቸር<br>በሲቪል ኢንጂነሪንግ<br>በስትራክቸራል ኢንጂነሪንግና<br>በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | ቢያንስ ሁለት | | |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በአርክቴክቸር<br>በሲቪል ኢንጂነሪንግ<br>በስትራክቸራል ኢንጂነሪንግና<br>በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | ቢያንስ አራት | | |
| 10 | የታሪካዊ ህንፃዎች ጥገናና እንክብካቤ ከዋኝ ባለሙያ (Building Conservator) | ጀማሪ ከዋኝ (ጠጋኝ) 1 | በቅርስ ጥበቃና<br>በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 5 - 8<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 3 -5<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | | | |
| | | ጀማሪ ከዋኝ (ጠጋኝ) 2 | በቅርስ ጥበቃና<br>በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው | ለዲፕሎማ 9 - 10<br>ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 6<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 3<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 0 | | | |
| | | ከዋኝ (ጠጋኝ) | በአርክቴክቸር<br>በሲቪል ኢንጂነሪንግ<br>በስትራክቸራል ኢንጂነሪንግና<br>በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 9 -10<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 6<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 4 | | | |
| | | ከፍተኛ ከዋኝ (ጠጋኝ) | በአርክቴክቸር<br>በሲቪል ኢንጂነሪንግ<br>በስትራክቸራል ኢንጂነሪንግና<br>በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው | ለመጀመሪያ ዲግሪ፡ 11<br>ለሁለተኛ ዲግሪ፡ 9<br>ለዶክትሬት ዲግሪ፡ 7 | | | |

# አባሪ 3 የማመልከቻ ቅጾች

## አባሪ 3.1 አዲስ የምስክር ወረቀት በሚጠይቅ አመልካች የሚሞላ

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን

የአገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ

<u>ለአዲስ  አመልካቾች</u>

1. ሙሉ ስም ---------------------------------------------------

2. አድራሻ

   ክልል----------------------------  ዞን--------------------------

   ወረዳ---------------------------- ከተማ-----------------------

   ክፍለከተማ--------------------------- ቀበሌ---------------------የቤ.ቁ----------------

   ስልክ የቢሮ----------------------- ሞባይል----------------------- ፋክስ--------------

   ኢ-ሜይል-------------------------------

3. አሁን የሚሰሩበት መስሪያ ቤት

   ስም፡

   አድራሻ፡

4. የትምህርት ደረጃ

| ተ.ቁ | ☐ተማሩበት ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ስም | የትምህርት መስክ | የትምህርት ደረጃ (ዲፕሎማ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ ዶክትሬት) |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |

5. የሥራ ልምድ

| ተ.ቁ | የስራ ሀላፊነት | ☐ሰሩበት ጊዜ | | ☐ሰሩበት መስሪያ ቤት ስምና አድራሻ |
|---|---|---|---|---|
| | | ከ | እስከ | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

6. የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች (መሰማራት ከሚፈልጉት ዘርፍ ጋር ግንኙነት ያለው)

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

7. የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት የሚፈልጉበት የቅርስ ጥበቃ ጉዳዮች

- የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥናት ☐
- የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ☐

8. የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት የሚጠይቁበት ዝርዝር የቅርስ ዘርፍ ጉዳይ

.......................................................................................................................................................

9. የጠየቁት የብቃት ደረጃ

ጀማሪ አማካሪ (ደረጃ 1) ☐

ጀማሪ አማካሪ(ደረጃ 2) ☐

ጀማሪ ከዋኝ(ደረጃ 1) ☐

ጀማሪ ከዋኝ(ደረጃ 2) ☐

አማካሪ ☐

ከዋኝ ☐

ከፍተኛ አማካሪ ☐

ከፍተኛ ከዋኝ ☐

10. የሚከተሉትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከቅጹ ጋር አብረው ያያይዙ

10.1. የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት

10.2. የትምህርት ማስረጃ

10.3. የዘረዘሩትን ስልጠናዎች ሰርተፊኬቶች

10.4. የተዘጋጁ ዘገባዎችና ዘገባዎቹን ማዘጋጀዎትን የሚያስረዳ ማስረጃ (ጀማሪ አማካሪና ከዋኝ አመልካቾችን አይመለከትም)

10.5. የስራ ልምድ ማስረጃ

10.6. አንድ ፎቶ ግራፍ

የአመልካች ስም ................................................ ፊርማ ......................... ቀን ..............................

## 3.1.2 . ደረጃቸውን ለማሳደግ በሚያመለክቱ አመልካቾች የሚሞላ

**በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን**
**አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ**
**ደረጃ ለማሳደግ**

1. ሙሉ ስም ---------------------------------------------------

2. አድራሻ

   ክልል---------------------------- ዞን--------------------------

   ወረዳ---------------------------- ከተማ-----------------------

   ክፍለከተማ--------------------------- ቀበሌ----------------------የቤ.ቁ----------------

   ስልክ የቢሮ----------------------- ሞባይል---------------------- ፋክስ---------------

   ኢ.-ሜይል------------------------------

3. አሁን የሚሰሩበት መስሪያ ቤት

   ስም፡

   አድራሻ፡

4. የትምህርት ደረጃ

| ተ.ቁ | ☐ተማሩበት ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ስም | የትምህርት መስክ | የትምህርት ደረጃ (ዲፕሎማ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ ዶክትሬት) |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |

5. የሥራ ልምድ

| ተ.ቁ | የስራ ሀላፊነት | ☐ሰሩበት ጊዜ | | ☐ሰሩበት መስሪያ ቤት ስምና አድራሻ |
|---|---|---|---|---|
| | | ከ | እስከ | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

6. የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች (መሰማራት ከሚፈልጉት ዘርፍ ጋር ግንኙነት ያለው)

...........................................................................................................

...........................................................................................................

7. ቀደም ሲል የብቃት ማረጋገጫ ያገኙበት የቅርስ ዘርፍ ጉዳዮች
   - የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥናት ☐
   - የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ☐

8. እንዲሰጥዎት የጠየቁት የብቃት ደረጃ

ጀማሪ አማካሪ (ደረጃ 1) ☐

ጀማሪ አማካሪ(ደረጃ 2) ☐

ጀማሪ ከዋኝ(ደረጃ 1) ☐

ጀማሪ ከዋኝ(ደረጃ 2) ☐

አማካሪ ☐

ከዋኝ ☐

ከፍተኛ አማካሪ ☐

ከፍተኛ ከዋኝ ☐

9. የሚከተሉትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከቅጹ ጋር አብረው ያያይዙ
   - 9.1. የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት
   - 9.2. የትምህርት ማስረጃ
   - 9.3. የዘረዘሩትን ስልጠናዎች ሰርተፊኬቶች
   - 9.4. የተዘጋጁ ዘገባዎችና ዘገባዎቹን ማዘጋጅዎትን የሚያስረዳ ማስረጃ (ጀማሪ አማካሪና ከዋኝ አመልካቾችን አይመለከትም)
   - 9.5. የስራ ልምድ ማስረጃ
   - 9.6. አንድ ፎቶ ግራፍ

የአመልካች ስም .................................... ፊርማ .................... ቀን ....................

## 3.1.3 እድሳት በሚጠይቁ አመልካቾች የሚሞላ ቅፅ

በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን
አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ
እድሳት ለሚጠይቁ

1. ሙሉ ስም --------------------------------------------------

2. አድራሻ

ክልል--------------------------- ዞን-------------------------

ወረዳ---------------------------- ከተማ----------------------

ክፍለከተማ--------------------------- ቀበሌ---------------------የቤ.ቁ----------------

ስልክ የቢሮ----------------------- ሞባይል---------------------- ፋክስ--------------

ኢ.-ሜይል------------------------------

3. አሁን የሚሰሩበት መስሪያ ቤት

ስም፡

አድራሻ፡

4. የትምህርት ደረጃ

| ተ.ቁ | ☐ተማሩበት ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ስም | የትምህርት መስክ | የትምህርት ደረጃ (ዲፕሎማ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ ዶክትሬት) |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |

5. የሥራ ልምድ

| ተ.ቁ | የስራ ሀላፊነት | ☐ሰሩበት ጊዜ | | ☐ሰሩበት መስሪያ ቤት ስምና አድራሻ |
|---|---|---|---|---|
| | | ከ | እስከ | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

6. የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች (መሰማራት ከሚፈልጉት ዘርፍ ጋር ግንኙነት ያለው)

.................................................................................................................................

.................................................................................................................................

7. የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት የሚፈልጉበት የቅርስ ጥበቃ ጉዳዮች

- የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥናት ☐
- የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ☐

8. የጠየቁት የብቃት ደረጃ

ጀማሪ አማካሪ (ደረጃ 1) ☐

ጀማሪ አማካሪ (ደረጃ 2) ☐

ጀማሪ ከዋኝ (ደረጃ 1) ☐

ጀማሪ ከዋኝ (ደረጃ 2) ☐

አማካሪ ☐

ከዋኝ ☐

ከፍተኛ አማካሪ ☐

ከፍተኛ ከዋኝ ☐

9. የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጠበት ቀን

.......................................................................

10. የሚከተሉትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከቅጹ ጋር አብረው ያያይዙ

10.1. የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት

10.2. የትምህርት ማስረጃ

10.3. የዘረዘሩትን ስልጠናዎች ሰርተፊኬት

10.4. የተዘጋጁ ዘገባዎችና ዘገባዎቹን ማዘጋጅዎትን የሚያስረዳ ማስረጃ (ጀማሪ አማካሪና ከዋኝ አመልካቾችን አይመለከትም)

10.5. የስራ ልምድ ማስረጃ

10.6. አንድ ፎቶ ግራፍ

የአመልካች ስም ......................................... ፊርማ ......................... ቀን .........................

## 3.1.4 ለጠፋ የምስክር ወረቀት ምትክ መጠየቂያ ቅፅ

በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባስልጣን
የአገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ
ለጠፋ የምስክር ወረቀት ምትክ ለሚጠይቁ

1. ሙሉ ስም -----------------------------------------------------

2. አድራሻ

ክልል---------------------------- ዞን--------------------------

ወረዳ---------------------------- ከተማ-----------------------

ክፍለከተማ---------------------------- ቀበሌ----------------------የቤ.ቁ----------------

ስልክ የቢሮ------------------------ ሞባይል----------------------- ፋክስ---------------

ኢ.-ሜይል-------------------------------

3. ቀደም ሲል ያገኙት የቅርስ ዘርፍ ጉዳዮች
   - የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ጥናት ☐
   - የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ☐

4. አግኝተውት የነበረው ደረጃ

ጀማሪ አማካሪ (ደረጃ 1) ☐

ጀማሪ አማካሪ(ደረጃ 2) ☐

ጀማሪ ከዋኝ(ደረጃ 1) ☐

ጀማሪ ከዋኝ(ደረጃ 2) ☐

አማካሪ ☐

ከዋኝ ☐

ከፍተኛ አማካሪ ☐

ከፍተኛ ከዋኝ ☐

5. የሚከተሉትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከቅጹ ጋር አብረው ያያይዙ

   5.1. የአመልካቹ የቀበሌ መታወቂያ

   5.2. ሰርተፊኬቱ ስለመጥፋቱ የሚያረጋግጥ የፖሊስ ማስረጃ

   5.3. አንድ ፎቶ ግራፍ

የአመልካች ስም ............................................ ፊርማ ...................... ቀን ...........................